# ሰማንያ ሚሊዮን ሕዝብ “ንጉስ” የሆነባት ሀገር

(ከአብዱራህማን አህመዲን፤ የቀድሞ የፓርላማ አባል)

(ይህ ጽሑፍ ነሐሴ 8 ቀን 2005 በወጣው ሰንደቅ ጋዜጣ ላይ ታትሟል፡፡ ጋዜጣውን የማያገኙ ሁሉ ቢያነቡት ‘ይጠቅማል፤ ለመወያያም መነሻ ሊሆን ይችላል’ በሚል መንፈስ በአይጋ ፎረም ድረ-ገጽ በኩል እንዲታተም ተልኳል፡፡)

ከግንባር መስመር ፖለቲከኛነት (Front Line Politics) ራሴን ማግለሌ የሚገርማቸው በቁጥር ጥቂት የማይሰኙ ወዳጆቼ፣ እንዲሁም የሚያውቁኝና የማያውቁኝ ያገሬ ሰዎች “ከፖለቲካ ለምን ወጣህ?” የሚል ተደጋጋሚ ጥያቄ ያቀርቡልኛል፡፡ እኔም ነገሩን በዋዛ ፈዛዛ፣ በሳቅ በፈገግታ ማለፍ ስለምፈልግ “ሰማንያ ሚሊዮን ሕዝብ ‘ንጉስ’ በሆነበት ሀገር ‘ንጉሰ ነገስት’ መሆን አስቸጋሪ ነው” የሚል ምላሽ መስጠትን አዘወትራለሁ፡፡

ጠያቂዎቼን የእኔ ከፖለቲካ መውጣት እንደሚያስገርማቸው ሁሉ፤ እኔን የሚገርመኝ ደግሞ እነዚህ ወገኖቼ “የፖለቲካ ክለብ” ጡረታ የማይወጣበት የዘላለም ርስት-ጉልት አድርገው የመቁጠራቸው አንደምታ ነው፡፡ እንዲህ ያለው አስተሳሰብ ‘የጥቂቶች’ ብቻ እንዳልሆነ ግምት በመውሰድ ነው ዛሬ ይቺን መጣጥፍ ለማሰናዳት ብዕር የጨበጥኩት፡፡

ብዙዎች እንደሚስማሙበት ፖለቲካ ጥበብ ነው፡፡ ፖለቲካ ሳይንስ ነው፡፡ ፖለቲካ እንጀራ የሚበላበት ሙያም ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ሰዎች በመስኩ ይሰማሩበታል፡፡ ይሳተፉበታልም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ጠቢቡ ሰለሞን “ለሁሉም ጊዜ አለው” እንዳለው፤ ሁሉም ነገር በጊዜ ገደብ የሚከወን በመሆኑ፣ ‘ፖለቲከኛነትም’ ዘላለማዊ የህይወት አካል ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም የሚል እምነት አለኝ፡፡ (የቀድሞ የትግል አጋሬ ልደቱ አያሌው ግን ደጋግሞ ‘ፖለቲከኛነት የህይወቴ አካል ነው’ ሲል ሰምቼዋለሁ)

እንደሚታወቀው ሾፌሩ፣ ቲያትረኛው፣ ስፖርተኛው፣ መሃንዲሱ፣ መምህሩ፣ ሀኪሙ፣... ዓመታትን ቆጥሮ፣ ጊዜውን ጠብቆ በጡረታ ይገለላል፡፡ ይሁን እንጂ፣ በጡረታ የተገለለ ሁሉ ከመብላትና ከመጠጣት በስተቀር ምንም ነገር አይሰራም፣ አይናገርም አይጋገርም ማለት ግን አደለም፡፡ አሰልጣኝነት ስራ ነው፡፡ ታሪክና ትውፊትን ማስተላለፍ ስራ ነው፡፡ በሀገር ሽማግሌነት የተጣላን ማስታረቅ፣ ማጋባትና ማፋታት ሥራ ነው፡፡ በሙያው አማካሪ ሆኖ መስራትም ሆነ መመራመር ሊከለከል አይችልም...ወዘተ.፡፡ ይህም በመሆኑ፤ ‘ጡረታ ወጡ’ ማለት ከግንባር መስመር ተሰላፊነት ተገለሉ ማለት እንጂ የጡረተኛነት ዘመን እርፍ የማይጨበጥበት፣ ብዕር ቀለም የማይጠጣበት፣ ተኝተው እንደ ሙሃቻ የሚውጡበት፣ ጊዜ በከንቱ የሚባክንበት... ዘመን ተደርጎ መወሰድ የለበትም፡፡

አዎ! ፖለቲከኛውም ቢሆን ጡረታ የማይወጣበት ምክንያት ሊኖር አይችልም፡፡ ይሁን እንጂ የኛ ሀገር ፖለቲከኞች ተገፍትረው ካልሆነ ‘በቃኝ’ ብለው ከፖለቲካው መድረክ ሲሰናበቱ ብዙም አይታዩም፡፡ እዚህ ላይ የሚያሳዝነው ነገር የፖለቲከኞቻችን ፖለቲካን ‘አለቅም’ ብለው “ሙጭጭ” ማለታቸው ብቻ አደለም፡፡ ይባስ ብሎ ፖለቲካችን የጡረተኞች መናኸሪያ፣ የስራ ፈቶች መቆዘሚያ መሆኑ ነው የሚያሳዝነው፡፡

አሳዛኝነቱ በዚህ አያበቃም፡፡ በተለይም በተቃዋሚው ጎራ ጡረተኛ ፖለቲከኞቹና ወጣት ፖለቲከኞቹ (ልክ እንደ አዲስ ገቢ ወይፈንና ለዘመናት ሲታረስ እንደኖረ በሬ) በተመጣጣኝ ደረጃ ሊያስቡና ተግባብተው ሊሰሩ ባለመቻላቸው፤ አዳዲስ ሃሰቦችን በማመንጨት ተከታታይነት ያለው ውጤት ማስመዝገብ ቀርቶ በተለያዩ አጋጣሚዎች የተገኙ ውጤቶች ጭምር የትም ተበትነው፣ መና ሆነው ቀርተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ተጨማሪ ኪሳራ፣ ሌላ አሳዛኝ ክስተት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡

ነገሩን በተጨባጭ ምሳሌ እንየው ከተባለ ከምርጫ 97 በኋላ በቅንጅት ውስጥ የታየው ሁኔታ ጥሩ አብነት የሚሆን ይመስለኛል፡፡ ‘ወጣቶቹ’ እና ‘ሽማግሌዎቹ’ ፖለቲከኞች በምርጫው ውጤትና ቀጣይ የፖለቲካ ሂደት ላይ የነበረን አቋም ልክ እንደ ወይፈኑና እንደ በሬው ‘እኩል መሳብ’ አልቻልንም ነበር፡፡ ወትሮም አዲስ ገቢ ወይፈንና ለዘመናት ሲታረስ የኖረ በሬ እኩል ሊስቡ አይችሉምና የሆነው ሁሉ መፈጸሙ አይቀሬ እንደነበር ቢታመንም፤ አእምሮ እያለን መደማመጥ አለመቻላችን ግን ያሳዝናል፣ ያስቆጫልም፡፡

ቅንጅት በፓርላማ ‘እንግባ - አንግባ’ አታካሮ እየተናጠ ባለበት ወቅት ለጦቢያ ጋዜጣ አንድ ቃለ ምልልስ ሰጥቼ ነበር፡፡ ጋዜጠኛ አጥናፉ አለማየሁ ባደረገልኝ ቃለ ምልልስ ቅንጅት ውስጥ የትውልድ ክፍተት መኖሩን ገልጬ፤ “የኢትዮጵያ ፖለቲካ ወደተሻለ ደረጃ እንዲሸጋገር ከተፈለገ በኢህአዴግም ውስጥ ይሁን በተቃዋሚው ጎራ ያሉ ከ50 ዓመት በላይ እድሜ ያላቸው ሰዎች ከፖለቲካው መድረክ መውጣት አለባቸው…” የሚል አስተያየት ሰንዝሬ ነበር፡፡

ጋዜጣው መስከረም 26 ቀን 1998 ዓ.ም ታተመ፡፡ መስከረም 28 የቅንጅት አመራር በፓርላማ መግባት እና አለመግባት አጀንዳ ዙሪያ ለመወያየት በኢዴፓ ጽ/ቤት በተገኘሁበት ወቅት የመጀመሪያውን የተቃውሞ ጠጠር የወረወረብኝ ዶ/ር በፈቃዱ ደግፌ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ ልክ እኔን ሲያይ የጓደኞቹን ስም እየጠራ ‘ከ50 ዓመት በታች ከሆንክ እንዳትጨብጠኝ…’ ይል ነበር ዶ/ር በፈቃዱ፡፡ ነገሩ እኔን ለማሸማቀቅ ነበር፡፡ እኔ ግን “ጎምቱዎቹ ፖለቲከኞች” በሰጠሁት ቃለ ምልልስ “ፀጉራቸውን ሊነጩ” እንደሚችሉ ቀድሜ የተገነዘብኩትና ያሰብኩበት ጉዳይ በመሆኑ በዶ/ር በፈቃዱ ሽሙጥ አልተሸበርኩም፡፡ እንዲያውም ‘የፀጉር መንጨቱ’ መገለጫ መሆኑን ነበር ያሰብኩት፡፡

ያኔ እኛ (ወጣቶቹ) ያልነውን ‘ታላላቆቻችን’ በሆደ ሰፊነት ሰምተውን ቢሆን ኖሮ የሀገሪቱ የተቃውሞ ፖለቲካ የኋሊት ተሸከርክሮ አሁን የሚታይበት ዘብጥ ላይ አይወርድም ነበር፡፡ ቅንጅትም እንደ መንፈስ ተኖ፣ እንደ ትቢያ ተበታትኖ ድራሹ አይጠፋም ነበር፡፡ የሚገርመው ከያኔው ስህተት የተማርን ባለመሆኑ የቅንጅት መበታተን ዛሬም አላቆመም፡፡

እንደ አሜባ ሴል መከፋፈሉ ቀጥሏል፡፡ ሰዎቹ እዚያ እስካሉ ድረስ ወደፊትም የሚቆም መሆኑ አይታየኝም - 'አንድ ሰው' እና 'አንድ ብዕር' እስኪቀር ድረስ ይቀጥላል ባይ ነኝ!!! እናም፤ እንደዚህ ዓይነት የህብረተሰብን ደምና ላብ መና ያስቀረ ኪሳራ ዳግም እንዳይከሰት ሁለት መፍትሄዎች ይታዩኛል፡፡ አንድም ቀዳሚውና ተከታዩ ትውልድ ተግባብተውና ተደማምጠው መስራት፤ አሊያም ቀዳሚው ትውልድ መስራት የሚችለውን ያህል ሰርቶ ለተከታዩ ትውልድ በማስረከብ ጡረታ መውጣት፡፡

አፈሩን ገለባ ያድርግላቸውና፣ ደራሲና ጋዜጠኛ ተስፋዬ ብርሃኑ እጄን ይዘው የጋዜጠኛነትን "ሀ-ሁ" ካስተማሩኝና ኮትኩተው ካሳደጉኝ የሥነ-ጽሁፍ መምህሮቼ አንዱና ቀዳሚው ናቸው፡፡ ጋሽ ተስፋዬ 'ዜና ቱሪዝም' ጋዜጣን ከሚያዘጋጁበት የደርግ ስርዓት ጀምሮ እስከ ሙዳይ መጽሔት ድረስ ከርዕሰ አንቀጽ ጀምሮ በተለያዩ ዘውጎች የተለያዩ መጣጥፎችን እንዳዘጋጅ አድርገውኛል፡፡ ጋሽ ተስፋዬ ጋር ለብዙ ዓመታት ሳንተያይ ቆይተን በአንድ አጋጣሚ መንገድ ላይ ተገናኘን፡፡ ከብዙ የናፍቆት ሰላምታ በኋላ "ጋሽ ተስፋዬ ምነው ሙዳይን ማተም አቆሙ?..." አልኳቸው፡፡ ፈገግ ብለው ትንሽ አዩኝና "... አስር ዓመት ሙሉ የምለውን አልኩ፡፡ ከዚህ በኋላ ቀደም ሲል ያልኩትን ደግሜ ከመጻፍ ውጪ የምለው አዲስ ነገር አይኖርም፡፡ ለአዲሱ ትውልድ መድረኩን መልቀቅ አለብኝ..." ነበር ያሉኝ፡፡

እንዳሉትም እሳቸውና የእሳቸው ዘመን ስሜት ቀስቃሽ (Sensational) ጋዜጠኞች መድረኩን ሲለቁ በርካታ ወጣት ጋዜጠኞች አዳዲስ አስተሳሰቦችን በአዳዲስ የአቀራረብ ስታይሎች አጅበው በማቅረብ የሀገሪቱን የጋዜጠኛነት ሙያ ወደ ላቀ ደረጃ ለማሳደግ (ድክመቶቻቸው እንደተጠበቁ ሆኖ) ጥረት አድርገዋል፤ እያደረጉም ነው፡፡ ከላይ የጠቀስኳትን የጋሽ ተስፋዬን አባባል ያቀረብኩትም ነባር ፖለቲከኞቹ ቦታውን ቢለቁላቸው አዳዲሶቹ ፖለቲከኞች የተሻለ ሥራ ሊሰሩ እንደሚችሉ ለማስረዳት ነው፡፡

ወደዚህ መጣጥፍ ርእስ እንመለስ፡፡ ከፖለቲካው ለምን ወጣህ ለሚሉኝ ወዳጆቼ "ሰማንያ ሚሊዮን 'ንጉስ' ባለበት ሀገር 'ንጉሰ ነገስት' መሆን አስቸጋሪ ነው" የሚል መልስ መስጠቴ ያለ ምክንያት አደለም፡፡ አንዳንድ ጊዜ 'እኛ ኢትዮጵያውያን ሁላችንም የንጉስነት መንፈስ በውስጣችን ያደረ' መሆኑን የሚያመላክቱ ሁኔታዎች እንደሚስተዋልብን አስባለሁ፡፡ እንዲህ ያለው "ጅምላ" አነጋገር ብዙዎችን እንደሚያበሳጭ ጥርጥር የለውም፡፡ ሐቁን ግን አያደበዝዘውም፡፡

የንጉስነት መንፈሱ በበርካታ መንገዶች የሚገለጽ መሆኑን በተጨባጭ ማሳየት ይቻላል፡፡ በመዲናችን አዲስ አበባም ይሁን በሌሎች ከተሞችና በገጠር መንደሮች ሳይቀር መሬት ያለው ሁሉ ቤት ሰርቶ ሲጨርስ የሚያጥረውን አጥር አስተውላችኋል? (አንዳንዱ ከቤቱ በፊት አጥሩን አጥሮ ሊሆንም ይችላል) አጥሩ ላይ የጠርሙስና የብረት እሾህ ይነሰነስበታል፡፡ እኔ እንዲህ ያለውን ሁኔታ ሳይ ሰንደቅ ዓላማ (ባንዲራ) ሰቅሎ አለማውለብለቡ ነው እንጂ 'ይህ የኔ ግዛት ነው' (This is my territory) የሚል

ይመስለኛል፡፡ እንዲህ ያለው ‘የግዛት’ መከለል እና ‘የወሰን’ ማስከበር ሁኔታ ደግሞ የንጉስነት መገለጫ አደለም ትላለችሁ?

በበኩሌ እንዲህ ያለው ከቤት የሚጀምር የንጉስነት መንፈስ ነው በፖለቲካችንም መንጸባረቁን ያስተዋልኩት፡፡ ምርጫ በሚካሄድበት ዓመት የሕዝብ ስሜት መነሳሳቱ የትም ሀገር የሚታይ የተለመደ ሁነት ነው፡፡ በሰለጠኑት ሀገሮች ፖለቲከኞቹ ሕዝቡን የመምራት (Leadership) ሚናቸውን በጥንቃቄና በብቃት ስለሚወጡና ሕዝቡም የተመሪነት ሚናውን ስለሚያውቅና ፖለቲከኞቹ በሚሰጡት አቅጣጫ ስለሚሄድ በመምራትም ሆነ በመመራቱ ሂደት የሚከሰት የሚና መፋለስና መደበላለቅ አይከሰትም፡፡ ቢከሰትም ወደ ትክክለኛው ሐዲድ ለመመለስ አያስቸግርም፡፡ በእኛስ ሀገር?

በእኛ ሀገር መምራትም መመራትም አስቸጋሪ ነገር ነው፡፡ በተለይ በምርጫ ሰሞንማ የፖለቲካ ተንታኙ ብዛት ለጉድ ነው፡፡ ፖለቲከኞቹን ‘እንዲህ አድርጉ፣ እንዲያ አታድርጉ፣ በዚያ ሂዱ፣ በዚህ ውረዱ...’ እያለ የሚያዘው “ንጉስ” ብዛት ወፈ-ሰማይ ነው፡፡ በፓርቲዎቹ ጽ/ቤት ተገኝቶ፣ አምስትም አስርም አዋጥቶ፣ በጠሩት ስብሰባ ላይ ተገኝቶ፣ ድጋፉንና ተቃውሞውን አሰምቶ፣... የማያውቀው አላፊ አግዳሚ ሁሉ ፖለቲከኞቹን ለማዘዝ ዱብ እንቅ ሲል ቅንጣት ታህል ቅር አይለውም፡፡

ዜጎች በማንኛውም ጉዳይ ላይ ሃሳባቸውን የማቅረብ፣ አስተያየት የመስጠትም ይሁን የመተቸት መብት እንዳላቸው አምናለሁ፡፡ ይሁን እንጂ፣ የአንድን ፓርቲ አመራር አካል ‘እንዲህ አድርግ፣ እንዲያ አታድርግ’ ብለው ሊያዙት የሚችሉት አባላቱ ብቻ (እነሱም ቢሆኑ በተስማሙበት ደንብ መሰረት) መሆኑን ማንም ልብ አይለውም፡፡ ቢለውም ደንታ የለውም፡፡ ታዲያ እንዲህ ያለው የአዛዥነት መንፈስ ከንጉስነታችን የሚመነጭ ፊላጭ ቆራጭነት አይደለም ትላላችሁ? ‘የቅንጅት አመራር’ የተደናበረው በእንደዚህ ዓይነት ስሜታዊ ጩኸት እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡

ታዲያ እንዲህ ያለው፣ እረኛው ግመሎቹን የሚመራበት ሳይሆን ግመሎቹ እረኛውን አስከትለው የሚሄዱበት ሁኔታ በፖለቲካው መድረክ መቆየትን ያስመኛል? አንዳንድ የዋሃን “ትግል ማለት እንዲህ ያለውንም አስተሳሰብ መታገል አደለም እንዴ?” የሚል ጥያቄ እንደሚያነሱ አስባለሁ፡፡ ትግሉ ባልከፋ! ግና ሁለት ስለት ባለው ሰይፍ ሲሄዱም ሲመለሱም መመተር ምን ያህል እንደሚያም የሚያውቀው የደረሰበት ብቻ ነው!

በኔ እምነት እንዲህ ያለው ሚናን ያለመለየት የ“ንጉስነት” መንፈስ ጥቂት የማይባሉ ፖለቲከኞቻችንን ተስፋ አስቆርጦ “ዳር ላይ ቁጭ ብሎ እንዳሻው የሚናገረው ሁሉ በሰው እጅ ላይ ሲያዩት የሚያምረውን አታሞ እስቲ ይግባና ይሞክረው” የሚል ድምዳሜ ላይ እንዳደረሳቸው እገምታለሁ፡፡ የሰዎች ተስፋ መቁረጥ ተገቢ ነው ባይባልም ስህተት ነው ለማለትም የሚቻል አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ሰማንያ ሚሊዮን ንጉስ ባለበት ሀገር ‘ንጉሰ ነገስት’ መሆን ቀርቶ “ባሪያ” ሆኖ ለማገልገልም እጅግ እጅግ አስቸጋሪ ነውና!

ጽሁፌን ለማጠቃለል አንዳንድ የመቋጫ ሃሳቦችን ላንሳ፡፡ በተለምዶ አነጋገር “ያ ትውልድ” የሚባለው ከእኛ የቀደመው ትውልድ በርካታዎቹ አባላቱ በተንኮል፣ በሸር፣ በሴራ፣… የተተበተቡ የክፋት አቂማዳዎች መሆናቸውን ተጨባጭ ማስረጃዎችን እያቀረቡ ማስረዳት ይቻላል፡፡ (ብዙዎቻችን የምናውቀው ስለሆነ ወደ ዝርዝር ጉዳይ መግባት የሚያስፈልግ አይመስለኝም)

እነዚህ ወገኖች ከሦስት ስርዓቶች (ከአፄው፣ ከደርግና ከኢህአዴግ) ጋር ሲታገሉ ኖሩ፡፡ ግና እርስ በርሳቸው ከመጫረስ ውጪ አንዳችም ያስመገቡት ድል የለም፡፡ በወጣትነትና በጎልማሳነት ዘመናቸው ያልቀናቸውን ድል ወደፊት ሊያስመዘግቡት ይችላሉ ብሎ ለመገመትም የሚቻል አይመስለኝም፡፡ ስለሆነም፣ እነዚህ ኃይሎች ከሀገሪቱ የፖለቲካ መድረክ ራሳቸውን ቢያገሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እፎይታ ብቻ ሳይሆን ትልቅ ውለታም ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

በአንጻሩ፣ የዚያ ትውልድ “የክፋት ቫይረስ” ወደ እኛ ትውልድ ጭምር የመሸጋገር ሁኔታ መኖሩን አስተውያለሁ፡፡ እናም፣ የፖለቲካውን መድረክ የእኛ ትውልድ ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጠረው ማለት ከታላላቆቻችን ወደ እኛ የተላለፈውን ክፋት፣ ተንኮልና ሸር ሁሉ ለተከታዮቻችን ማሸጋገራችን አይቀሬ ነው የሚል ስጋት አለኝ፡፡ እናም፣ ይህ ከመሆኑ በፊት በኔ የእድሜ ክልል የምንገኝ ጎልማሳ ፖለቲከኞች ጭምር (ሙሉ ለሙሉም ባይሆን) ከግንባር መስመር ፖለቲካው ዘወር ብንል ለሀገራችን የወቅቱ ፖለቲካ እፎይታ እንደሚሆን አስባለሁ፡፡ አበው፣ ‘የሀገሩን በሬ በሀገሩ ሰርዶ’ እንዲሉ፤ የወቅቱን ፖለቲካ ለአዲሱ ትውልድ ብንተውለት ለዚህ ዘመን የሚመጥን ትግል ሊያደርግ እንደሚችል ጥርጥር የለውም ባይ ነኝ፡፡

ይህንን በዚህ እንተወውና ወደ ሌላ ጉዳይ እናምራ፡፡ በአንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ ውስጥ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በተናጠል የሚጫወቷቸው ሚናዎች አሏቸው፡፡ በዚህም መሰረት የህዝብ ሚና፣ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ሚና እና የፓርቲ መሪዎች ሚና ግልጽ በሆነ መልኩ ተለይተው ሊታወቁና ሁሉም ወገን የየድርሻውን ኃላፊነት በአግባቡ ሊወጣ ይገባል፡፡ አንዱ የሌላውን ሚና ነጥቄ እጫወታለሁ፣ ያሻኝ ቦታ እየገባሁ እፈተፍታለሁ የሚል ከሆነ ግን በዚች አገር ፖለቲካ የሚባል ነገር ዓይነቱ እንደጠፋ ልቃቂት ሊፈታ በማይችል መልኩ መወሳሰቡ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡

አንዳንድ የፖለቲካ ሳይንስና የሕግ ምሁራን እንደሚሉት ከሆነ ለአንድ ሀገርና ሕዝብ እጅግ አስፈላጊ ናቸው ከሚባሉት ነገሮች አንዱ ፖለቲካ ነው፡፡ ዶክተር ባይኖር በዳማ ከሴውም በፌጦውም መታከምና ሕይወትን መቀጠል ይቻላል፡፡ ሕግ ባይኖር በባህል፣ በልማድም ሆነ በሃይማኖት እየተዳኙ መኖር ይቻላል፡፡ ፍልስፍና፣ ታሪክ፣ ጂኦግራፊ፣ ማኔጅመንት፣ ፊዚክስ፣ ባዮሎጂ፣ ጂኦሎጂ፣ ኢንጅነሪንግ፣… ቲያትረኛ፣ ጋዜጠኛ፣ ስፖርተኛ፣… እና ሌሎችም ሙያዎችና ሙያተኞች ኖሩም አልኖሩ ሕይወት ያን ያህል የከፋ አደጋ ላይ አይወድቅም፡፡ ማህበረሰብም አገርም መኖር ይችላሉ፡፡ ያለ ፖለቲካ ግን ቢውሉ ማደር፣ ቢያድሩ መዋል አስቸጋሪ ነው፡፡ ቢኖርም የሰቆቃ ኑሮ ነው፡፡ እሱም ረጅም

ጊዜ ሊቆይ አይችልም፡፡ (ለዚህ አባባል አብነት ይሆነን ዘንድ የሶማሌያውያንን የሃያ ዓመታት ሕይወት ማየቱ ጠቃሚ ነው)

ስለሆነም፣ ለሕልውናችን አስፈላጊ የሆነው ፖለቲካና ፖለቲከኞች ተገቢውንና ተፈላጊውን እንቅስቃሴ ማድረግ ይችሉ ዘንድ እያንዳንዱ ዜጋ የየድርሻውን ሚና በተገቢው መንገድ ሊወጣ ይገባዋል፡፡ ሁሉም ሰው ፖለቲከኛ፣ ሁሉም ሰው ንጉስ፣ ሁሉም ሰው ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ፕሬዝዳንት፣... መሆን አይችልም፡፡ መላው ሕዝብ በተስማማባቸው ሕጎች መሰረት ጥቂቶች አመራር ይሰጣሉ፡፡ በተስማማነው መሰረት እየተመራን መሆኑን ግን ሁላችንም የማረጋገጥና በቀጣዩ አመራር ማንነት ላይ የመወሰን ኃላፊነት ይኖረናል፡፡ የሰለጠነ ሕብረተሰብ የሕይወት ፍልስፍና ከዚህ ውጪ ሊሆን እንደማይገባው አስባለሁ፡፡